# ከሌሎች ጋር ትንሽ አብረን እንዋል

ሕሊና ነጋሣ
ከእስከመቼ አዘጋጆች
መስከረም ፳፻፫ ዓ. ም.

ከወዳጆቻችን ጋር አብረን እየዋልን፣ እርስ ለራሳችን የምንፅፈውን እየተናበብንና፣ ያንኑ የአምና ያቻምና አታሞ እየደለቅን፤ ያገር ጥሪን ማስተናገድ አንችልም። አዕምሮን አስፍተን፣ የማያዋጣ መንገድን ወደጎን ትተን፣ አዲስ መንገድ ለመቀየስና፣ ባዲስ መንፈስ ወደፊት ለመጓዝ፤ ከመሠሎቻችን ጋር ብቻ ሣይሆን ከሌሎች ጋርም የግድ አብረን መዋል አለብን። በየምሽጋችን አድፍጠን ከሌሎች ጋር መተባበር አንችልም። የራሳችንን እንጠብቃለን ብለን እግሮቻችንን ባለንበት አንፈራጠን ወደሌሎች ሠፈር መጓዝ አንችልም። ጥሪ መወርወር ፈቃደኛ ናቸው አያሰኝም። የዚህ ፅሑፍ መልዕክት፤ ለሀገር አቀፉ ሀገር አድን ጥሪ፤ እስኪ መጀመሪያ የሌላ ሠፈር አባሎች ከምንላቸው ጋር፤ ጥቂት አብረን እንዋል ነው።

<u>ሀቁን እናሥፍረው</u>፤

፩ኛ. ብዙ በቆየን ቁጥር የፖለቲካው ግማት፤ እንኳንስ ቀና አመለካከት ኖሯቸው ወደ ሕዝቡ ሠፈር ለመቀላቀልና የሕዝቡን ትግል ለመደገፍ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱትን ይቅርና፤ አሁን በትግሉ ላይ ያሉትን አንገፍግፎ ያባርራቸዋል። ይህ ደግሞ የመለስ/ህወሀት ምኞት ነው።

፪ኛ. የመለስ/ህወሀት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ባህሪው ነውና፤ ሀገር አጥፊ፣ ሕዝብን በታኝ፣ ሰላምን በጥባጭ ነው። እናም መደራደር፣ ከእምነቱ ፈቀቅ ማለት፣ ትንሽም ቀዳዳ መንገድ መስጠት፤ በጭንቅላቱ ከያዘው የመዝገበ ቃላቱ ውጪ ነው።

፫ኛ. ባሁኑ ሰዓት ተባብረው ካልተነሱ ትግሉን በግል የትም ማድረስ እንደማይቻል ያልተቀበለ፤ በትግል ላይ ሣይሆን በእንቅልፍ ላይ ነውና፤ ንቃ በሉት።

፬ኛ. ሀገር አቀፉ ግንባር፤ ባንድ ጥሪና ባንድ ምሽት እንዳይመሠረት እኛው እንቅፋቶች ደርድረናል። ስለዚህ ምኞቱን ትተን ሃቁን እንቀበል። ይህ የምኞት ሣይሆን የባህሪያችን ተገዥ ክንውን ነውና! **ከድርጅቶች ውጭ የሆነ የሽምግልና አካል ያስፈልገናል።** በድርጅት ያልታቀፉችሁና ይኼን የምታነቡ ሁሉ፤ ኃላፊነቱ በኛችሁ ነው።

፭ኛ. የወቅቱ አጀንዳ ነጥሮ ከፊታችን እያለ፤ በማያንገበግበው ጉዳይ ማተኮሩ፤ ላለመተባበር ምክንያት ማብዛት ነው። የግል አጀንዳ፣ የቡድን አጀንዳ፣ የድርጅት አጀንዳ አሁን የለም። አሁን ያለው የሀገር አድን አጀንዳ ብቻ ነው። ይህን አጀንዳ ደግሞ በግል በባለቤትነት የያዘ የለም። አጀንዳው የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀብት ነው። እንደ ሀገሪቱ።

*<u>ታዲያ እንዴት እንጀምረው</u>*?

*ከሁሉ በፊት መቅደም አለበት የምንለው፤ በአንድነት ሀገሪቱን ማዳኑ ወሳኝ መሆኑን የተረዳ ሁሉ፤ በፈቃደኝነት መነሣት ነው። እናም የተለያዩ ድረ ገፆችን ጎብኙ። በተለያዩ የፓልቶክ ክፍሎች ግቡ። ያላዳመጣችሁትን የሬዲዮ ሥርጭት ክፈቱና አዳምጡ። በማንኛውም የሕዝቡ ወገን የሆነ ስብሰባ ተገኙ። መገኘቱና መከታተሉ ብቻ በቂ አይደለም። በድፍረት የምታምኑበትን ሃሳብ አቅርቡ። ተቃዋሚ አለ። ባለጌም አይጠፋም። የያዛችሁትን አቋም ያመናችሁበትና ለኢትዮጵያ የሚበጃት ትክክለኛ መፍትሄ ብላችሁ የምታራምዱት እስከሆነ ድረስ፤ ዝልፊያውና ከክፍል መባረሩ ሊያስደነግጣችሁ አይገባም። ዕድልም አለማግኘት ያጋጥማል። ክፍሎቹና ድረ ገፆቹ ራሳቸው በዚሁ ሂደት ላይ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። መማማርን ቅድሚያ እንስጠው።*

*ግትር ሆነው እኛ የወደድነውን ዓይነት ብቻ ነው የምናስተናግደው ከሚሉ ድረ ገፆችንና የፓል ቶክ ክፍሎች ሂዱና ተነታረኩ አንልም። ከወያኔ ደጋፊ ጋር ተወያይቶ አንድ ሃሳብ ላይ የመድረስ ሕልሙ ሰዓቱ እንዳለፈበት ሁሉ፤ የእኛን መፍትሄ ብቻ አቀንቅኑ ከሚሉ ጋርም፤ በየትኛውም ጎራ ራሳቸውን ይመድቡ፤ ውይይት አድርጎ አንድ መፍትሄ ላይ መድረስ አይቻልም።*

*<u>ማጠቃለያ</u>*፤

*በኛ እምነት*፤

*ሀ) የእያንዳንዳችን መነሣትና በድፍረት የምናምንበትን፤ በፈቃደኝነት ከመሰሎቻችን ጋር ብቻ ሣይሆን፤ ከማንም ሀገር ወዳድና የተለየ ሀሳብ ይዘው ለመወያየት ግን ፈቃደኛ ከሆኑ ኢትዮጵያዊያን ጋር መወያየቱ መሠረታዊና የግድ አሥፈጊ ግዴታ ነው እንላለን።*

*ለ) ጎን ለጎን ደግሞ፤ ያለንበት ፈታኝ የትግል ወቅት፤ አደገኛና ወሳኝ መሆኑን የተገነዘቡና ከድርጅቶች ውጭ ያሉ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን፤ ኃላፊነቱ በጃቸው እንደሆነ ተገንዝበው የማሰባሰቡን ተልዕኮ መጀመር አለባቸው። እኛ በምንችለው ለመርዳት ዝግጁ ነን።*

*ሐ) እስካሁንም እየተሠራ ያለበትና አሁንም በመተግበር ያለው የድርጅቶች መፈላለግ መቀጠል አለበት። በእርግጥ ይህ የሚያጠያይቅና የሌሎችን ግፊት የሚያስጠብቅ ጉዳይ አይደለም። ባሁኑ ወቅት ግን፤ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶበት፤ መቀራረቡ እንዲፋጠን እናሳስባለን።*

*<u>ማስመልከቻ</u>*፤

*ትብብርን አስመልክቶ ከተለያዩ ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች የተለያየ ግንኙነቶች እንድናደርግ ተጠይቀናል። እንዳቀራረባቸውም መልስ እየሰጠን ነው። በፈቃደኝነት መንገዱን አብረን ከመጥረግ አንስቶ እስከ በግሥጋሴው አለመጣጣም የተነጋገርናቸው አሉ። በአጠቃላይ ወቅቱ በሁላችንም ዘንድ የፈጠረው መነሣሣት ከፍተኛ ነው።*

*ሕሊና ነጋሣ*
eske.meche@yahoo.com